በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማ እና ትንበያ መጽሔት

## ከሜይ 21-31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ እንዲሁም

## ከጁን 1-10 እና ከጁን 11-20/2024

## የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ጁን 2024

አዲስ አበባ

ስልክ +251115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ርዕስ ገፅ

**እ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ** - 1 -

ምስል 1 የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ - 2 -

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ - 3 -

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት - 3 -

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር - 3 -

እ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ - 4 -

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ - 4 -

እ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ - 5 -

- 5 -

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ - 5 -

እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ - 6 -

ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከጁን 1-10, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ - 7 -

ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከጁን 1-10, 2024 የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን - 7 -

ካርታ 8 እ.ኤ.አ. ከጁን 1-10, 2024 የሚኖረዉ ከፍተኛ የአየር የሙቀት መጠን በዲ.ሴ - 7 -

እ.ኤ.አ ከጁን 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ - 7 -

ካርታ 9 እ.ኤ.አ ከጁን 11-20፣ 2024 - 8 -

የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ - 8 -

እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ - 8 -

እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ - 9 -



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፉት የሜይ ሶስተኛው አስራ አንድ ቀናት በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብ እንዲሁም በመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተጠናከረ የደመና ሽፋን ከመኖሩ ጋር ተያይዞ በብዙ ስፍራዎቻቸው ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል በአሊያ 38.5 እና 47.2፤ በበደሌ 42.8 እና 43.6፤ በዲላ 34.4፤ በዶሎመና 45.2፤ በጋቲራ 31.6፤ በላይበር 38.5 እና 71.7፤ በጊዳ አያና 50.0፣ በሊሙ ገነት 34.3፤ በማሻ 78.0፤ በሞጣ 49.2፤ በነጆ 35.2፣ በነቀምቴ 67.0 እና 57.6፣ በአርጆ 36.6፣ በጊምቢ 37.9፤ በቴፒ 33.2፤ በወላይታ ሶዶ 99.9 እንዲሁም በሳውላ 64.4 በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡


ባለፉት ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል ባሌ፣ ምዕራብ እና ደቡብ ምዕራብ ሸዋ፣ ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ኢሉባቦር እና ጅማ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ማዕከላዊ እና ደቡብ ጎንደር፣ አዊ ዞን፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጀም እና የሰሜን ሸዋ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳ እና ካማሺ ዞኖች፤ ከጋምቤላ ክልል ኑዌር እና ማዣንግ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ሀላባ፣ ከምባታ እና ጠምባሮ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጋሞ፣ ጎፋ፣ ኮንሶ፣ ባስኬቶ፣ ቡረጂ፣ ደራሼ፣ ደቡብ ኦሞ እና ወላይታ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች ላይ ከ51-200 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ4-9 ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፣ ከሱማሌ ክልል ፋፋን፣ አፍዴር፣ ሊበን እና ዳዋ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል ቦረና፣ ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ምስራቅ እና ሰሜን ሸዋ(ሰላሌ)፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ሀሪ ዞን፤ ከትግራይ ክልል ምዕራብ እና ደቡብ ምስራቅ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን እና የምዕራብ ጎንደር ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ እና የኢታንግ ልዩ ዞን ላይ ከ5-15 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ1-3 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡



ስልክ +251115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከኦሮሚያ ክልል ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ምዕራብ እና ደቡብ ምዕራብ ሸዋ፣ ባሌ እና ምዕራብ አርሲ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ቅልበቲ ዞን፤ ከትግራይ ክልል ምስራቅ እና ደቡብ ምስራቅ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ምዕራብ እና ደቡብ ጎንደር፤ ዋህግምራ፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ አዊ ዞን፣ ሰሜን ሸዋ፣ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳ እና ካማሺ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀላባ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ጠምባሮ እና የየም ልዩ ዞን፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ባስኬቶ፣ ጎፋ፣ወላይታ፣ ደራሼ፣ ጋሞ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች እንዲሁም ሀረር ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን አግኝተዋል (ካርታ 3) ፡፡


በሌላ በኩል በሰሜን ምስራቅ፣ በምስራቅ፣ በደቡብ ምስራቅ እና ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ36.4-43.8 ዲግሪ ሴልሽየስ ተመዝግቧል (ምስል 1) ፡፡





ምስል 1 የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ




ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 1 ኢ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

ካርታ 2 ኢ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት





ካርታ 3 ኢ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# እ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባባለፉት ቀናት በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከእርጥበታማ (moist) እስከ በጣም እርጥበታማ (Humid) ሁኔታ አመዝኖባቸው እንደነበረ የተተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ይህም ሁኔታ እድገታቸውን ላልጨረሱና በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበልግ ሰብሎች፣ ለጓሮ አትክልቶችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ በተጨማሪም ከኤፕሪል ጀምሮ ለተዘሩ እንደ ቦቆሎና ማሽላ ለመሳሰሉ የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎች ጠቀሜታው የጎላ ነበር፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የተገኘው እርጥበት ለአርብቶ አደርና ከፊል የአርብቶ አደር አካባቢዎች ላየ የግጦሽ ሳርናና የመጠጥ ውኃ አቅርቦትን ከማሻሻል አንጻር አዎንታዊ ሚና የነበረው። በሌላ በኩል በብዙ የመኸር አብቃይ አካባቢዎች ላይ የተገኘው እርጥበት አስቀድመው የማሳ ዝግጅት እንዲያከናውኑና ጠቀሜታ ነበርው(ካርታ 4) ፡፡





ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ቀናት በአባይ፣ ተከዜ፣ ባሮአኮቦ፣ ኦሞጊቤ፣ የስምጥ ሸለቆ የላይኛው አፋር ደናክል፣ ዋቤ ሸበሌ፣ የገናሌ ዳዋና የኦጋዴን ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ መጠን ያለው እርጥበት ነበራቸው። ይህም ሁኔታ የገፀ ምድር የውሃ ሀብትን እና የግድቦችን የውሃ አቅም ከማሻሻል አንጻረ አዎንታዊ ሚና ነበርው (ካርታ 5) ።




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ


በመደበኛ ሁኔታ የክረምት ዝናብ በጁን በመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት የደቡብ ምዕራብና የምዕራብ የሀገሪቱን አከባቢዎች ጨምሮ ቀስ በቀስ የሰሜን ምዕራብ ክፍሎችን የሚያዳርስበት ጊዜ ነው ።

በሚቀጥለው አሥራ ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለይም በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የዝናብ መጠንና ሥርጭት እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከዚሁ ጋር በተያያዘም እርጥበታማው የአየር ሁኔታ ከቀን ወደ ቀን በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብና በሰሜን ምዕራብ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ በመጠንም ሆነ በሥርጭት እየተስፋፋ ከመሄዱ ጋር ተያይዞ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 6)፡፡


በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋ፣ ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ኢሉባቦር፤ ከአማራ ክልል ማዕከላዊ እና ምዕራብ ጎንደር፣ አዊ ዞን፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳ፣ ካማሺ፣ መተከል እና የማኦ ኮሞ ልዩ ዞን፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ባስኬቶ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ወላይታ እና ጌዲዮ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ሀላባ፣ ሃዲያ፣ ጠምባሮ እና የየም ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል ማዣንግ፣ አኝዋክ፣ የኢታንግ ልዩ ዞን እና ንዌር ዞኖችላይ የተሻለ የዝናብ መጠንና ስርጭት ይኖራቸዋል (ካርታ 6 )፡፡ በተጨማሪም ከኦሮሚያ ክልል ባሌ፣ ምዕራብ እና ደቡብ ምዕራብ ዞኖች፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ ፤አዲስ አበባ፣ ድሬ ዳዋ እና ሃረር ከአማራ ክልል ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ ደቡብ ጎንደር፤ ከትግራይ ክልል ምዕራብ እና ሰሜን ምዕራብ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንሶ፣ አማሮ፣ አሌ፣ ቡርጂ፣ ደራሼ፣ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ስልጤ፤ ቀላል መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6)፡፡ በሌላ በኩል የቀኑ ከፍተኛ ሙቀት በሰሜን ምሥራቅ እና በምስራቀ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ ከ35 ዲግሪ ሴልሺየስ በላይ እንደሚሆን አሃዛዊ ትንበያዎች ያመላክታሉ (ካርታ 8)።




ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከጁን 1-10, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከጁን 1-10, 2024 የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን




ካርታ 8 እ.ኤ.አ. ከጁን 1-10, 2024 የሚኖረዉ ከፍተኛ የአየር የሙቀት መጠን በዲ.ሴ

## እ.ኤ.አ ከጁን 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ


በጁን ሁለተኛው አሥር ቀናት በመደበኛ ሁኔታ በደቡብ ምዕራብ" በምዕራብ" በሰሜን ምዕራብና በመካከለኛው አካባቢዎች ላይ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች እየተጠናከሩ የሚሄዱ ሲሆን፤ በአንጻሩ በሰሜንና በሰሜን ምሥራቅ ላይ አልፎ አልፎ ከሚኖረው መጠነኛ ዝናብ በስተቀር ደረቅና ሞቃታማ የአየር ሁኔታ ያመዝናል፡፡

በመጪዉ የጁን ሁለተኛዉ አስር ቀናት ለክረምት ዝናብ መፈጠር አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከቀን ወደ ቀን እየተሻሻሉ ከመሄዳቸው ጋር ተያይዞ፤ በደቡብ ምዕራብ፣ በመካከለኛዉ፣ በምዕራብ እና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 9) ፡፡



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

Rainfall performance (mm) for 11-20 June 2024




ካርታ 9 እ.ኤ.አ ከጁን 11-20፣ 2024

የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት በተለይም በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል፡፡ ይህም ሁኔታ አስቀድመው ተዘርተው በተለያየ የዕድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበልግ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎችና ለጓሮ አትክልቶች የውሃ ፍላጎትን ከማሟላት አኳያ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም በጁን ወር ለሚዘሩ የመኸር ሰብሎች የማሳ ዝግጅት ለማከናወንም ሆነ የተዘጋጁ ማሳዎችን በሰብል የመሸፈን ተግባራትን ለማከናወን አዎንታዊ ሚና ስለሚኖረው አርሶ አደሮች ይህንኑ መልካም አጋጣሚ ለመጠቀም የሚያስችል ዝግጅት ከወዲሁ ማከናወን ያስፈልጋል፡፡



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ  ከጁን 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት በአብዛኛው አባይ፣ ተከዜ፣ አዋሽ፣ ባሮአኮቦ፣ ኦሞጊቤ፣ አፋር ደናክሌ፣ የላይኛው እና የመካከለኛው የስምጥ ሸለቆ፣ የላይኛው ዋቤ ሸበሌና የገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ የእርጥበት ሁኔታ ይኖራቸዋል፡፡ ይህም ሁኔታ ተፋሰሶች የተሻለ የውሃ መጠን እንዲኖራቸው ከማድረግ አንጻር አዎንታዊ ሚና የሚኖረው ሲሆን በተጨማሪም ለመስኖም ሆነ ለሀይል ማመንጫነት የሚያገለግሉ ግድቦችን የውሃ መጠን ከመጨመር አንጻር አዎንታዊ አስተዋጽዖ ይኖረዋል፡፡



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066  ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et